የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ታኀሣሥ ፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 3
ADDIS ABABA 18th December, 2013


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፩/፪ሺ፮ ዓ.ም

የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ አዋጅ......................ገጽ ፯ሺ፩፻፲፭


## አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፩/፪ሺ፮

## የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የወጪና ገቢ ምርቶችን በተመጣጣኝ የትራንስፖርት ዋጋ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጓጉዘው ወደ ወደብ እንዲደርሱ ወይም ከወደብ ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተሰራጭተው ለተጠቃሚው እንዲቀርቡ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በጭነት ላኪዎችና ተረካቢዎች፣ የመጫኛና የማራገፊያ አገልግሎት በሚሰጡ መጋዘኖች እና ቁጥጥር በሚያከናውኑ አካላት የአሰራር ቅልጥፍና መጓደል ምክንያት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የሥራ ጊዜ ከፍተኛ ብክነት የሚታይበት በመሆኑ፤

ይህን የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የሥራ ጊዜ ብክነት በማስቀረትና ምልልስን በማፋጠን ጭነት የማንሳት አቅምን ለማሳደግ እንዲሁም የዕቃዎችን የወደብ ቆይታ ጊዜ በማሳጠር አላስፈላጊ ወጪን ለመቀነስና ተያያዥ ችግሮችን ለማስወገድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያን የሚደነግግ ህግ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዲመሬጅ ክፍያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፩/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

CONTENTS


Proclamation No. 811/2013

Trucks Demurrage Proclamation ......... Page 7115


## PROCLAMATION No. 811/2013

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR TRUCKS DEMURRAGE

WHEREAS, it has become necessary to transport export and import goods with appropriate cost and within short period of time to the port or from port to consumer distribution channels across the country;

WHEREAS, the inefficiencies of shippers and consignees, warehouses providing loading and unloading facilities and regulatory bodies conducting inspection are resulting in considerable time loss in truck operations;

WHEREAS, it has become necessary to enact a legislation on trucks demurrage to avoid such loss of time in truck operations and to increase the frequency of use of trucks and thereby increase freight carrying capacity and shorten the waiting time of goods at ports to minimize unnecessary costs and to avoid related problems;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE

## GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Trucks Demurrage Proclamation No. 811/2013".


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.20

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩/ "የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ" ማለት ማንኛውንም ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ጐታች መኪናን ይጨምራል፤

፪/ "ዕቃ" ማለት የቁም እንስሳትን ጨምሮ ኮንቴነሮችን፣ የዕቃ ማሸጊያዎችን ወይም ተመሳሳይ የዕቃ ማሸጊያ ቁሶችን ወይም በዕቃ ላኪው ወይም በዕቃ አስረካቢ በጥቅል መልክ ለጭነት የሚቀርብ ማንኛውም ንብረት ነው፤

፫/ "አጓጓዥ" ማለት ዕቃን በተሽከርካሪ አማካኝነት በየብስ ወይም በአገር ውስጥ ውሃ የሚያጓጉዝ ሰው ነው፤

፬/ "ላኪ" ማለት ለራሱ ወይም ለሦስተኛ ወገኖች ሲል ዕቃውን እንዲያጓጉዝ ለአጓጓዡ የሚያስረክብ ሰው ነው፤

፭/ "ተረካቢ" ማለት ዕቃውን ለመቀበል ህጋዊ መብት ያለው ሰው ነው፤

፮/ "መጋዘን" ማለት ማንኛውም ብትንም ሆነ ጥቅል ዕቃዎችን በኮንቴነር ጭምር የመጫኛና የማራገፊያ አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ቦታ ሆኖ ወደብንና የጉምሩክ መጋዘንን ይጨምራል፤

፯/ "አሽከርካሪ" ማለት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ለመንዳት የሚያስችለው ህጋዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ሰው ነዉ፤

፰/ "ዲመሬጅ" ማለት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን፡-

ሀ) በላኪ፣ በተረካቢ ወይም በመጋዘን ለመጫኛ ወይም ለማራገፊያ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ፣ ወይም

ለ) በመንግሥት ተቆጣጣሪ አካል ለሚካሄድ የቁጥጥር ሥራ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ፤

እንዲቆይ በመደረጉ ለባከነው ጊዜ ማካካሻ የሚፈጸም ክፍያ ነዉ፤

## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ "truck" means a motor vehicle constructed or adapted for use and used primarily for the conveyance of goods of any description and includes a truck tractor;

2/ "goods" means any property including live animals as well as containers, pallets or similar articles of transport or packaging supplied by the sender or consignor;

3/ "carrier" means a person who performs the carriage of goods by land or internal waters;

4/ "sender" means a person who, either for his own account or for that of third parties, delivers goods to the carrier for carriage;

5/ "consignee" means a person authorized to receive the goods;

6/ "warehouse" means any place, including port and customs warehouse, that provides loading and unloading facilities including packed and unpacked goods in container;

7/ "driver" means an individual who holds the required driving license to drive trucks;

8/ "demurrage" means a payment to compensate for detaining a truck beyond the time limit allowed:

a) for loading or unloading by a sender, consignee or warehouse; or

b) for inspection conducted by a government regulatory body;

፱/ “የመጫኛ ወይም የማራገፊያ ጊዜ” ማለት የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ለመጫን ወይም ለማራገፍ የተወሰነለት ቦታ ከደረሰ በኋላ ጭነቱን ለመጫን ወይም ለማራገፍ የሚወስደው ጊዜ ሲሆን ተፈላጊ ሰነዶች ተጠናቀዉና ተፈርመው አሽከርካሪው የሚረከብበትን ጊዜ ያጠቃልላል፤

፲/ “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደምተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፩/ “ባለስልጣን” ማለት በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ የተቋቋመው የትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤

፲፪/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፫/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በጭነት ላኪዎች፣ ተረካቢዎች፣ የመጫኛና የማራገፊያ አገልግሎት በሚሰጡ መጋዘኖች፣ የፍተሻና የቁጥጥር ስራ በሚያከናውኑ አካላት፣ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ ትራንስፖርተሮች እና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የመጫኛ፣ የማራገፊያና የቁጥጥር ጊዜ ገደብ እና የዲመሬጅ ክፍያ

## ፬. የመጫኛና የማራገፊያ ጊዜ ገደብ

፩/ ማንኛዉም ላኪ፣ ተረካቢ ወይም የመጋዘን አገልግሎት የሚሰጥ አካል፡-

ሀ) የመጫን አቅሙ ፳ ቶን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በ፰ ሰዓት ውስጥ የመጫን ወይም በ፮ ሰዓት ውስጥ የማራገፍ፤ ወይም

9/ “period of loading or unloading” means the time required for loading or unloading of a truck after its arrival at the place specified for loading or unloading and includes the time required for handing over to the driver the fully completed and signed documents;

10/ “Ministry” or “Minister” means the Ministry or Minister of Transport, respectively;

11/ “Authority” means the Transport Authority established under the Transport Proclamation No. 468/2005;

12/ “person” means any natural or juridical person;

13/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable on shippers, consignees, warehouses providing loading and unloading facilities, bodies conducting search and inspection activities, transporters engaged in truck operations and trucks.

## PART TWO

## TIME LIMIT FOR LOADING, UNLOADING AND INSPECTION AND PAYMENT OF DEMURRAGE

## 4. Time Limit for Loading and Unloading

1/ Any sender or consignee or warehouse operator shall have the obligation:

a) to load within 8 hours and unload within 6 hours a truck with loading capacity of 20 tons or above; or

ለ) የመጫን አቅሙ ከ፳ ቶን በታች የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በ፭ ሰዓት ውስጥ የመጫን ወይም በ፬ ሰዓት ውስጥ የማራገፍ፤

ግዴታ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረዉ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዉ የመጫኛ ወይም የማራገፊያ ቦታው እንደደረሰ ይሆናል፡፡

፫/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው የመጫኛ ወይም የማራገፊያ ቦታው ከደረሰ በኋላ ከአጓጓዡ ጋር ባልተያያዘ ምክንያት የመጫኛ ወይም የማራገፊያ ቦታ ለውጥ ከተደረገ በለውጡ ምክንያት የባከነው ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተካቶ ይታሰባል፡፡

፭. <u>የቁጥጥር ጊዜ ገደብ</u>

፩/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የጫነውን ዕቃ በመግቢያ ወይም በመውጫ በር ወይም በመተላለፊያ መንገድ ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥር በአንድ ሰዓት ውስጥ እንዲሁም በመዳረሻ የጉምሩክ ጣቢያ የሚያደርገውን ከአራት ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት፡፡

፪/ የግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ኳራንቲን ጣቢያ፡-

ሀ) የአንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን ንጽህና እና ምቹነት የማረጋገጥ ስራ በ፴ ደቂቃ ዉስጥ፤

ለ) በአንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የተጫኑ እንስሳትን የጤና ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መስራትና መስጠት በሦስት ሰዓት ውስጥ፤

ሐ) የአንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን የመኖ የይለፍ ሰርተፍኬት መስራትና መስጠት በ፴ ደቂቃ ውስጥ፤

ማጠናቀቅ አለበት፡፡

b) to load within 5 hours and unload within 4 hours a truck with loading capacity of less than 20 tons.

2/ The time limit referred to in sub-article (1) of this Article shall begin to run from the time of arrival of the truck at the place of loading or unloading.

3/ If there is a change on the place of loading or unloading after the arrival of a truck at the place of loading or unloading for reasons not attributable to the carrier, the extra time spent due to the change shall be included in the calculation of the period referred to in sub-article (1) of this Article.

5. <u>**Time Limit for Inspection**</u>

1/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall conduct inspection of goods loaded on a truck within one hour at port of entry or exit or transit route, or in less than four hours at the destination customs station.

2/ Any animal quarantine station of the Ministry of Agriculture shall:

a) conduct a truck sanitation and suitability inspection within 30 minutes;

b) prepare and issue animal health certificate with respect to animals loaded on a truck within three hours;

c) prepare and issue animal feed pass certificate with respect to animal feed loaded on a truck within 30 minutes.

፫/ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የአንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን የክብደት ሚዛን ቁጥጥር በ፳ ደቂቃ ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት፡፡

፬/ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በንግድ ሚኒስቴር ወይም የተቆጣጣሪነት ሥልጣን ባለው የሚመለከተው ሌላ መንግሥታዊ አካል የሚካሄድ አንድ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ የጫነውን ዕቃ የመቆጣጠር ሥራ በሦስት ሰዓት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ (፫) እና (፬) የተመለከተው የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው ቁጥጥር ወደሚደረግበት ጣቢያ እንደደረሰ ይሆናል፡፡

፮. <u>የመጫኛ፣ የማራገፊያና የቁጥጥር የሥራ ሰዓት</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት የመጫንና የማራገፍ አገልግሎት የሚሰጥ መጋዘን ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት ቁጥጥር የሚያካሂድ ማንኛውም ተቆጣጣሪ አካል ከሰኞ እስከ እሁድ ፳፬ ሰዓት ሙሉ ይህንኑ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

፯. <u>የዲመሬጅ ክፍያ</u>

፩/ ማንኛውም ላኪ፣ ተረካቢ ወይም የመጋዘን አገልግሎት የሚሰጥ አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ በተደነገገው መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ፡-

ሀ) የመጫን አቅሙ ፳ ቶን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በሚመለከት፡-

(፩) ለመጀመሪያ ሁለት ሰዓት የባከነ ጊዜ በሰዓት ብር ፩፻ ሂሳብ፣

(፪) ከሁለት ሰዓት በላይ እስከ አራት ሰዓት ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር ፩፻፶ ሂሳብ፣

(፫) ከአራት ሰዓት በላይ ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር ፪፻ሂሳብ፣ ወይም

3/ The Ethiopian Roads Authority shall undertake truck weight inspection process within 20 minutes.

4/ The Ministry of Health, Ministry of Agriculture, Ministry of Trade or any other concerned government regulatory body shall conduct inspection of goods loaded on a truck within three hours.

5/ The time limit referred to in sub-article (1), (2), (3) and (4) of this Article shall begin to run from the time of arrival of the truck at the station where the inspection is conducted.

6. <u>Working Hours for Loading, Unloading and Inspection</u>

Any warehouse engaged in loading and unloading operations in accordance with Article 4 of this Proclamation or any regulatory body conducting inspection in accordance with Article 5 of this Proclamation shall provide such service for 24 hours from Monday to Sunday.

7. <u>Demurrage</u>

1/ Any sender, consignee or warehouse operator who has failed to meet its obligations as stipulated under Article 4 of this Proclamation shall pay demurrage to the carrier on the following basis:

a) with respect to a truck with loading capacity of 20 tons or above:

(1) Birr 100 per hour for the first two hours delay;

(2) Birr 150 per hour for the delay of more than two hours up to four hours;

(3) Birr 200 per hour for the delay of more than four hours; or

ለ) የመጫን አቅሙ ከ፳ ቶን በታች የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በሚመለከት፡-

(፩) ለመጀመሪያ ሁለት ሰዓት የባከነ ጊዜ በሰዓት ብር ፸፭ ሂሳብ፤

(፪) ከሁለት ሰዓት በላይ እስከ አራት ሰዓት ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር ፻ ሂሳብ፤

(፫) ከአራት ሰዓት በላይ ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር ፻፶ ሂሳብ፤

የዲመሬጅ ክፍያ ለአጓጓዡ መክፈል አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ቁጥጥር የሚያካሂድ አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ በተደነገገው መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ፡-

ሀ) የመጫን አቅሙ ፳ ቶን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በሚመለከት ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር ፻ ሂሳብ፤ ወይም

ለ) የመጫን አቅሙ ከ፳ ቶን በታች የሆነ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን በሚመለከት ለባከነ ጊዜ በሰዓት ብር ፸፭ ሂሳብ፤

የዲመሬጅ ክፍያ ለአጓጓዡ መክፈል አለበት፤ ሆኖም የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪው ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ እንዲቆይ ሊደረግ የቻለው መቅረብ የሚገባው የጭነት ማጓጓዣ ሰነድ በአጓጓዡ ባለመቅረቡ ምክንያት ከሆነ የዲመሬጅ ክፍያ ሊጠየቅ አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የዲመሬጅ ክፍያ ተግባራዊ የሚሆነው በቀን ለ፲ ሰዓት ብቻ ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከሚወሰነው የዲመሬጅ ክፍያ በላይ የሆነ ጉዳት የደረሰበት አጓጓዥ በማጓጓዣ ውሉና አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጨማሪ የጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

b) with respect to a truck with loading capacity of less than 20 tons:

(1) Birr 75 per hour for the first two hours delay;

(2) Birr 100 per hour for the delay of more than two hours up to four hours;

(3) Birr 150 per hour for the delay of more than four hours.

2/ A body conducting inspection which has failed to meet its obligations as stipulated under Article 5 of this Proclamation shall pay demurrage to the carrier for the delay on the following basis:

a) Birr 100 per hour with respect to a truck with loading capacity of 20 tons or above; or

b) Birr 75 per hour with respect to a truck with loading capacity of less than 20 tons;

provided, however, that no demurrage may be payable where the detention of the truck beyond the specified time limit is caused by failure of the carrier to present the required consignment note.

3/ The demurrage payable pursuant to sub-article (1) and (2) of this Article shall apply only for 10 hours per day.

4/ A carrier who has sustained more damages than the demurrage determined pursuant to sub-article (1) of this Article shall have the right to claim the excess on the basis of his contract of carriage and the appropriate law.

፭/ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪን ለመጫን ወይም ለማራገፍ ወይም ለቁጥጥር ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት እንዲቆይ ያደረገ የመንግሥት መጋዘን ወይም የተቆጣጣሪ አካል ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት በአሠሪው የተፈጸመን የዲመሬጅ ክፍያ የመተካት ኃላፊነት አለበት፡፡

**፰. <u>የመጫኛ፣ የማራገፊያና የቁጥጥር ጊዜ ማረጋገጫ ሰነድ</u>**

፩/ ማንኛውም ላኪ፣ ተረካቢ፣ መጋዘን ወይም ተቆጣጣሪ አካል የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ በመጫኛ፣ በማራገፊያ ወይም በመቆጣጠሪያ ቦታ የደረሰበትንና አጠናቆ የወጣበትን ቀንና ሰዓት ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቅጽ ላይ መዝግቦ ከአሽከርካሪው ጋር መፈራረም አለበት፡፡

፪/ አሽከርካሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተመዘገበው ቀንና ሰዓት የማይስማማ ከሆነ ልዩነቱን አስፍሮ ሰነዱን መፈረምና ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለሥልጣኑ የትራንስፖርት ኢንስፔክተር ወይም በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፳፬ መሠረት በባለሥልጣኑ ውክልና ለተሰጠው አካል ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ሪፖርት የደረሰው የትራንስፖርት ኢንስፔክተር ወይም ውክልና የተሰጠው አካል ጉዳዩን አጣርቶ የምርመራ ውጤቱን የያዘ ማስረጃ ለሚመለከታቸው ወገኖች ይሰጣል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፱. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ባለስልጣኑ፡-

፩/ ይህ አዋጅ በሚገባ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

5/ Any employee or officer of a government warehouse or a regulatory body who has, intentionally or by negligence, detained a truck beyond the time limit specified for loading or unloading or for inspection shall be liable to reimburse the demurrage paid by his employer in accordance with sub-article (1) or (2) of this Article.

**8. <u>Document Evidencing Loading, Unloading and Inspection Period</u>**

1/ Any sender, consignee, warehouse operator or regulatory body shall register the date and time of arrival of a truck at a place for loading, unloading or inspection and the completion of the operation on a form prepared for such purpose and counter sign same with the driver.

2/ If the driver disagree with the date and time registered in accordance with sub-article (1) of this Article, he shall sign the document by entering his reservations, and report same immediately to the nearest transport inspector of the Authority or to the organ delegated by the Authority pursuant to Article 24 of the Transport Proclamation No. 468/2005.

3/ The transport inspector or the delegated organ that has received a report in accordance with sub-article (2) of this Article shall investigate the case and issue the concerned parties with evidence containing its findings.

## <u>PART THREE</u>

## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**9. <u>Powers and Duties of the Authority</u>**

The Authority shall:

1/ follow up and supervise the proper implementation of this Proclamation;

፪/ እንደአስፈላጊነቱ በጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የመጫኛ፣ የማራገፊያና የመቆጣጠሪያ ቦታዎች የትራንስፖርት ኢንስፔክተሮች ይመድባል፤

፫/ ሞዴል የጭነት ማመላለሻ ውልና የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ቅጾችን ያዘጋጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን የጭነት ማጓጓዣ ታሪፍ በማጥናት የውሳኔ ሃሣብ ያቀርባል፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

## ፲. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም ህግ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ፲፩. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፪. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፱ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ assign transport inspectors, as deemed necessary, at the places for loading, unloading and inspection of trucks;

3/ prepare and distribute to the concerned bodies model contract for freight transport and trucks movement monitoring formats;

4/ undertake study and submit proposal on freight tariffs for trucks, when deemed necessary, and follow up the implementation of same upon approval by the Council of Ministers.

## 10. Inapplicable Laws

No law or customary practice may, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

## 11. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

## 12. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 18th day of December, 2013.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት